# የACPS Express 9/16/2022: ACPS፣ የሂስፓኒክ ማህበረሰባችንን በዓል-ያከብራል

## ACPS፣ የሂስፓኒክ ማህበረሰባችንን በዓል-ያከብራል



በአሌክሳንድሪያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools (ACPS) ውስጥ፣ ብሄራዊ የሂስፓኒክ ተወላጅነት (National Hispanic Heritage) ወርን - በማክበሩ-ደስተኛ ነው! በACPS ውስጥ፣ ወደ 38% የሚጠጉት ተማሪዎቻችን የሂስፓኒክ ተወላጆች ሲሆኑ፣ ይህም ከፍተኛ-ቁጥር የሆነው የስነ-ሕዝብ (demographic) ቡድንን የሚወክል ነው። በእያንዳንዱ ዓመት፣ የሂስፓኒክ እና የላቲኖ አሜሪካውያንን የዘር-ግንዳቸው - ከማዕከላዊ አሜሪካ (Central America)፣ ደቡብ አሜሪካ (South America)፣ ካረቢያን (the Caribbean)፣ ሜክሲኮ (Mexico) እና ስፔን (Spain) - ወደ አሜሪካ ከመጡ ጋር፣ ባህሎቻቸውን እና ያበረከቱትን-አስተዋጽዖ ለማክበር፤ ከሴፕቴምበር (Sept.) 15 እስከ ኦክሮበር (Oct.) 15 ድረስ - እንደ ማህበረሰብ በአንድ-ላይ ሆነን-እንሰበሰባለን። የዚህ ዓመት ገጽታ-የሆነው (This year’s theme)፤ “Unidos: Inclusivity for a Stronger Nation” ነው።

የሂስፓኒክ ሄሪቴጅ ሣምንት (Hispanic Heritage Week)፣ በመጀመሪያ የታወጀው፣ በፕሬዚዳንት ሊንዶን ጆንሶን (President Lyndon Johnson) በ1968 ዓ.ም ነበር። ከዚያም፣ በ1988 ዓ.ም በፕሬዚዳንት ሮናልድ ሬገን (President Ronald Reagan) ጊዜ የ30-ቀን ጊዜን ለመሸፈን ተስፋፍቷል። በሴፕቴምበር 15 ቀን ላይ፣ አንዳንድ በማዕከላዊ እና በደቡብ አሜሪካ አገራቶች ውስጥ - ኮስታ ሪካ፣ ኤል ሳልቫዶር፣ ጓቴማላ፣ ሆንዱራስ፣ እና ኒካራጉዋን ጨምሮ - የነፃነት-በዓላቸውን የሚያከብሩበት ነው። በተጨማሪም፤ ሜክሲኮ (Mexico) እና ቺሌ (Chile) - የነፃነት ቀን-በዓላቸውን በሴፕቴምበር (Sept.) 16 ቀን እና በሴፕቴምበር (Sept.) 18 ቀን - እንደየአቀማመጣቸው-ያከብራሉ። የሃገሬ-ተወላጅ ሰዎች (Indigenous Peoples) ቀን፤ እና ‘Día de la Raza’ በዓላት፤ በዚሁ በ30-ቀን ጊዜው ውስጥ የሚውሉ-ናቸው።

የሂስፓኒክ ሄሪቴጅ (Hispanic heritage)፣ ከማዕከላዊ እና ደቡብ አሜሪካ ወደ እዚህ በመጡ ነዋሪዎች ረጅም-ታሪክ ያለው ሲሆን፣ አሌክሳንድርያን ለመቅረጽ-እርዳታ ያደረገ ነው። ከኤል ሳልቫዶር (El Salvador) የመጡ ከፍተኛ-የማህበረሰብ ቁጥር-ያላቸው፣ በ1980ዎቹ ውስጥ፤ በኤል ሳልቫዶር ከተማ-በተሰየመው - ‘ቺሪላጉዋ (Chirilagua)’ ተብሎ-አሁን በሚጠራው - አጎራባች-ቦታ ላይ ሰፍረው-ነበር። በእንግሊዘኛ፣ ስፓኒሽ ቋንቋዎች፣ ስለዚህ ሰፈራ-ምንነት፤ በCultural History of Arlandria-Chirilagua ላይ የበለጠ ለማወቅ ማግኘት ትችላላችሁ። ብሄራዊ የሂስፓኒክ ሄሪቴጅ ወር (National Hispanic Heritage Month) በሚከበር-ጊዜ፣ የAlexandria Library፤ ስለሂስፓኒክ አሜሪካውያን ታሪክ እና ያበረከቱትን አስተዋጽዖ የበለጠ-ለመዳሰስ የሚያስችሉ - የመጽሐፍት ምርጫዎችን እና የመረጃ-ስብስቦች (databases)ንም አጉልቶ-የሚያቀርብ ይሆናል።

በACPS ውስጥ በመሆን፤ ሁላችንም በአንድነት በዚህ ወር ውስጥ በርካታ የሂስፓኒክ አሜሪካውያን ማህበረሰባችንን ለማክበር፣ ከታሪካቸው ለመማር እና ባህላቸውን ለማክበር አብረን-በህብረት እንሰበሰባለን። በACPS በወሩ ሙሉ ውስጥ፣ ዝግጅቶችን የሚያዘጋጅ እና የመረጃ-ምንጮችን የሚያጋራ ይሆናል። የብሄራዊ የሂስፓኒክ ሄሪቴጅ ወር ገጽታ-የሆነው (theme) አጥብቆ-የሚያሳየው፤ ጠንካራ ለሆነ ሃገር ሁሉን-አካታች መሆን ያለውን ጥቅም፣ እና ይህም የACPS እና የ2025 ስልታዊ ዕቅድ (Strategic Plan) በትምህርት ቤት ክፍል/division ዙሪያ በዚሁ መርህ መሠረት ወደፊት-ለመግፋት እንደሚሰራ ያሳያል።

## በአጋርነት እና በጎ-ፍቃደኝነት (Partner and Volunteer) ላይ ጉልህ-ነገሮች: ሁለት የብሄራዊ የሂስፓኒክ ሄሪቴጅ ወር አጋርነቶች




የ'Hispanic Heritage' ወርን - ከሴፕቴምበር (Sept.) 15 - ኦክሮበር (Oct.) 15 ድረስ በአሌክሳንድሪያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools (ACPS) ውስጥ በሚከበር ጊዜ፤ የሂስፓኒክ አሜሪካውያንን ለሃገራችን እና ለማህበረሰቡ ያበረከቱትን አስተዋጽዖ እውቅና-የሚሰጥበት ጊዜ ነው። በሴፕቴምበር የአጋርነት ታሪካችን ውስጥ፤ ሁለት ለረጅም-ጊዜ የቆዩ የACPS የማህበረሰብ አጋሮችን - የአሌክሳንድርያ አካባቢን በማገልገል የቆዩ - ካሳ ቺሪላጉዋ (Casa Chirilagua) እና 'Liberty's Promise'ን አጉልተን-የምናሳይ፣ እና በማህበረሰባችን ውስጥ የሂስፓኒክ ታዳጊ የወደፊት ትውልዶችን ለማነቃቃት እንደረዳ ያበረከቱት ስራ-ላይ ትኩረት እንሰጣለን።

"Kids Club፣ Teens Club እና Casa to College — የአመራር ቧንቧ-መስመራችን (leadership pipeline) ብለን የምንጠራውን የሚያጠቃልልን-ነው፤" ብለው የካሳ ቺሪላጉዋ (Casa Chirilagua) ዋና አስተዳዳሪ የሆኑት - አድሪአና ጎሜዝ ሼልሃስ (Adriana Gomez Schellhaas) ገልጸዋል። እነዚህ ፕሮግራሞች፤ በበርካታ የእድሜ ቡድኖች ውስጥ የሚገኙ የቀለም-ትምህርት እርዳታን የሚያገኙን - በንባብ እና በቤት-ስራ እርዳታን ጨምሮ፤ እርዳታ-መስጫ ቦታን የሚያዘጋጅ ነው። በተጨማሪም፤ ተማሪዎች የበለጠ እራሳቸውን-እንዲያውቁ እና ያላቸውን ጭንቀት እና ግጭት መቆጣጠር እንዲችሉ ለመርዳት - የመማሪያ ዕድሎችን ያቀርባሉ። ካሳ ቺሪላጉዋ (Casa Chirilagua)፣ ወጣት ሰዎች - ያላቸው ድምጽ-ግድ እንደሚል እና እንዴት በትክክለኛ-ሁኔታ መጠቀም እንደሚችሉ እንዲገነዘቡ ይረዳል። "እኔ በውሳኔዬ እና በቃላቶቼ ላይ ኃላፊነት አለኝ የሚል-ይሆናል፤" ብለዋል ጎሜዝ ሼልሃስ (Gomez Schellhaas)።

የካሳ ቺሪላጉዋ (Casa Chirilagua) ተቀጣሪዎች - ታሪካዊ የሆነው አቀራረባቸው፤ ከአጠቃላይ ቤተሰቡ ጋር ግንኙነቶችን በመፍጠር - በአሌክሳንድርያው አርላንድሪአ አካባቢ (Alexandria's Arlandria area) ውስጥ በሚሰጡት አዎንታዊ የሆነ ከትምህርት-በኋላ (after-school ) እንቅስቃሴዎች በሚሰጥ-ጊዜ ይጠቀመዋል።

[Kids Club] - ከ1-5 ክፍሎች ውስጥ ለሆኑ ተማሪዎች ነው፤ በሂሳብ እና በንባብ እርዳታን ይሰጣል፣ የኮምፒውተር ልምድን፣ የአካል-ንቅናቄ እና በስነጥበባት (arts) ውስጥ እንቅስቃሴዎችን ይሰጣል። [የ'Teens Club' እና 'Casa to College'] ዕድሜያቸው-ከፍ ላለ ተማሪዎች ነው። የ'Teens Club'፣ ለመካከለኛ ደረጃ (Middle) ትምህርት ቤት ተማሪዎች - ከማህበራዊ እና የዕድገታዊ እርዳታ ጋር - በቡድን ክፍሎች እና በአገልግሎት-መማሪያ ፕሮጀክቶች (group classes and service-learning projects) አማካኝነት - የምሽት እና የቅዳሜና እሁድ ከትምህርት-እንቅስቃሴ ውጪ (extracurricular) የሆኑ ዕድሎችን ይሰጣል። 'Casa to College'፣ የተዘጋጀው ለከፍተኛ ደረጃ ተማሪዎች በ2018 ውስጥ ሲሆን፣ ለእነዚህ የዕድሜ ቡድን በካሳ ቺሪላጉዋ (Casa Chirilagua) ውስጥ ለማሟላት የሚረዳ ነው። ለወደፊት ስኬት፣ ለኢንተርንሽፕስ (internships)፣ ለኮሌጅ ጉብኝቶች - በዚህ ሂደት ውስጥ ያሉ ቤተሰቦችን ጨምሮ፤

የሚያዘጋጅ - የሙያ-ስልጠና ትምህርት ችሎታዎችን ይሰጣል። ጎሜዝ ሼልሃስ (Gomez Schellhaas) እንደአጠቃለሉት: “በ‘Casa’ የተሰጠው የመካሪነት-አገልግሎት (mentorship) ዋጋው-ተተምኖ አያልቅም።”



*በካሳ ቺራላጉዋ (Casa Chiralagua) ፡የሕፃናት ክለብ (Kids Club ̈ የ5ተኛ ክፍል የምርቃት ዝግጅት ጊዜ፤ ተማሪው ከቤተሰቦቹ ጋር የተነሳው ፎተግራፍ።*

ለታዳጊ ስደተኞች ደራሽ-የሆነ ሌላ ድርጅት፤ Liberty's Promise ነው። ድርጅቱ የሚሰጣቸው ፕሮግራሞች፤ እንደ Civics and Citizenship ያሉ፤ በእንግሊዘኛ የሚሰጡ፣ እና Civic Engagement for Beginning English Language Learners (CE-BELL) በስፓኒሽ-ቋንቋ የሚገኙ ናቸው። “እኛ የምናወራው ስለ የሰብዓዊ ተሳትፎ ነው፣ ነገር ግን የማህበረሰብ ተሳትፎንም እንደ አንድ-እኛ ዋናው ገጽታችን (one of our core themes) አድረገን ነው፤” ብለው ገልጸዋል - መሊሳ ጉሬሮ ጌሊናስ (Melissa Guerrero Gelinas)፣ የኖርዘን ቨርጅኒያ እና የዋሽንግተን ዲሲ የ‘Liberty’s Promise’ የፕሮግራሞች ዳይሬክተር።

ጉሬሮ ጌሊናስ (Guerrero Gelinas) ጨምረው-ሲገልጹ፤ እነዚህ ፕሮግራሞች ለታዳጊ-ስደተኞች፣ ዕድሜያቸው ከ15-21 ለሆኑ፤ ጥንካሬአቸው እና የባህል-ስብጥራቸ ዋጋ-የተሰጠው መሆኑን - በራሳቸው-መተማመን እንዲሰማቸው እና እንዲያውቁ ያደርጓቸዋል። እነዚህ ፕሮግራሞች - ለታዳጊ ስደተኞች፤ እንዴት መንግሥት እንደሚሰራ እና እነሱን የሚወክላቸው ማን እንደሆነ፣ እና በአሌክዳንድርያ ማህበረሰብ ዝግጅቶች እንደ ፓርክን ማጽዳት (park clean-ups) ባሉ ዝግጅቶች ውስጥ እንደሚያሳትፉቸውም፣ ገልጸዋል። ‘Liberty’s Promise’፣ በተጨማሪም - ታዳጊ ስደተኞቹ፣ ወደ ከፍተኛ ትምህርት እንዲቀጥሉ እና ወደ ትምርጉም-ሰጪ የስራ-መስኮች እንዲሰማሩ እንዲገፉበትም ይረዱዋቸዋል።

በከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ስኬታቸው ላይ ማስፋፋትን ለማቅረብ፣ ‘Liberty’s Promise’፣ አሁን-ሁለተኛ ዓመቱ የሆነውን በ‘ቦልቲሞር ካውንቲ (Baltimore County)’ ውስጥ የፓይለት-የመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ፕሮግራም የሆነው - ፕሮግራም አለው። የዚህን ፕሮግራም - በፍራንሲስ ሲ. ሃመንድ (Francis C. Hammond) መካከለኛ ደረጃ (Middle) ትምህርት ቤት እና ጆርጅ ዋሽንግተን (George Washington) መካከለኛ ደረጃ (Middle) ትምህርት ቤት ውስጥ፤ ማስፈለግን-የተመለከቱ መሆናቸውን - ጉሬሮ ጌሊናስ (Guerrero Gelinas) በመግለጽ፤ ድርጅታቸው ይህ ለአነስተኛ የእድሜ ቡድን ውስጥ ለሚገኙ ለአሌክሳንድርያ - በ2023-24 የትምህርት ዓመት ውስጥ ሊሆኑ ለሚችሉ - ይህን ፕሮግራም ለማምጣት ዓላማው አድርጎ-እንደሚሰራ ገልጸዋል። በመካከለኛ ደረጃ (Middle) የትምህርት ቤት ደረጃ ውስጥ የሚገኙ ተማሪዎችን ማዳረስ — የስራ-መስክ ግቦቻቸው ላይ እንዲደርሱ የቀለም-ትምህርት ላይ ትኩረት ማድረግ — ወደ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እና ከዚያም-ባለፈ ሁኔታ - በቀላሉ ዝውውር ለማድረግ እንደሚረዳቸው፤ እምነታቸው እንደሆነ ተናግረዋል።

ሌላ የ‘Liberty’s Promise’ ፕሮግራም የሆነው - Opportunities Plus ነው። ስራ-የመስራት ፈቃድ ያላቸውን ታዳጊዎችን ዕድል-የሚሰጥ እና በአነስተኛ የቤተሰብ-ገቢ የሚኖሩን በኢንተንሽፕ (internship) ምደባን - በትርፍ-አልባ ድርጅቶች (nonprofits)፣ ማዘጋጃ-ቤት እና በአካባቢ-የንግድ-አውታሮች ውስጥ መመደብ-ያቀርባል። ከተሳትፎው አስቀድሞ፣ ተማሪዎች ጠንከር-ባለ የስራ-ችሎታዎች አውደ-ጥናት ላይ፣ የሬዙሜ (resume) እና አብሮ-የሚላክ ደብዳቤ (cover letter) አፃፃፍን መማር፣ የቃለ-መጠይቅ ችሎታዎችን መቆጣጠር እና ስለየስራ-ቦታ ባህል መማርን ባሉት አውደ-ጥናት ውስጥ ይካፈላሉ።



*ተማሪዎች፤ የስሚትሶኒያ ብሄራዊ የዙዮሎጂካል ፓርክ (Smithsonian's National Zoological Park)ን እንደ ‘ Liberty's Promise Civic Engagement’ በማድረግ ለእንግሊዘኛ ቋንቋን-ለሚማሩ ፕሮግራም ጀማሪዎች - ጉብኝት አድርገዋል*

የACPS አጋርነት - እንደ ካሳ ቺሪላጉዋ (Casa Chirilagua) እና ‘Liberty’s Promise’ ያሉት፤ የትምህርት ቤት ክፍል/divisionን ለመርዳት እና ፍትሃዊ-ትምህርትን ለሁሉም ተማሪዎች በማቅረብ ግቡ ላይ ለመድረስ እንዲችል ለማርዳት አሁንም-ቢሆን ሌላ የማጓዣ-መንገዱ ነው። ከማውንት ቨርነን ኮሚውኒቲ (Mount Vernon Community) ትምህርት ቤት ጋር በመስራት፣ ጎሜዝ ሼልሃስ (Gomez Schellhaas) እንዳሉት - በትምህርት ቤት ሠራተኛ እና በቤተሰብ መካከል ግንኙነትን መገንባት - ምርጥ-የሆነ ትምህርታዊ ውጤቶችን ለማግኘት - ጠቃሚ-መሆኑን መገንዘባቸውን ገልጸዋል። በተጨማሪም፤ ACPS ቤተሰቦች በአፍ-መፍቻ ቋንቋቸው ግንኙነት እንዲያደርጉ ለማስቻል - የትርጉም አገልግሎቶችን በማቅረቡ፣ ጥቅም-መገኘቱን አስምረውበታል። ጎሜዝ ሼልሃስ (Gomez Schellhaas) እንዳሉት፤ ይህ ተማሪዎች ላይ ተጽዕኖ ሊያሙቱ የሚችሉ ነገሮች ላይ፣ ቤተሰቦች እንዲመዝኑ ይረዳቸዋል። በመጨመርም፤ ልክ እንደ ACPS ሁሉ፤ ለአስፈላጊ-የሆነ ማህበራዊ፣ ስሜታዊ፣ እና የቀለም ትምህርት (Social, Emotional, and Academic Learning (SEAL) - ተማሪዎችን ለስኬት ስለሚረዳ - ካሳ ቺሪላጉዋ (Casa Chirilagua) - በበኩሉ ቁርጠኝነቱን ያሳያል።

ጉሬሮ ጌሊናስ (Guerrero Gelinas) እንዳሉት፤ በ“መጫወቻ-ሜዳም ላይ ቢሆን እንኳ፣” ከትምህርታዊ እርዳታ ባለፈ-ሁኔታ የተስፋፋ የኔትወርክ እርዳታን መስጠት ጠቃሚ-ነው ብለዋል። ተመሳሳይ የቀደመ-መነሻዎች (backgrounds) ካሏቸው መካሪዎች (mentors) ጋር፣ ታዳጊ-ስደተኞች እንዲተዋወቁ ማድረግ፣ የእነርሱ የሕይወት ህልም እንደ-ማሳያና ማበረታቻ እንዲሆንላቸው በማድረግ፤ እነርሱም በትምህርት እና ከዚያም-ባለፈ-ሁኔታ ስኬትን ለማግኘት እንደሚያስችላቸው ያምናሉ። ጉሬሮ ጌሊናስ (Guerrero Gelinas) ጨምረው-ሲገልጹ፤ ታዳጊዎችን ስለሚኖራቸ ዕድሎች በማስተማር - ‘Liberty’s Promise’፣ በትምህርት ቤት መገኘት (attendance) ላይ፣ በራስ-መተማመን፣ እና በውጤት-ደረጃዎች በተሳታፊ-ተማሪዎች መካከል መጨመሩን አይቷል።  እና፣ በፕሮግራሙ ውስጥ ያሉ የታዳጊ ተመራቂ መጠን፣ በአሌክሳንድርያ ፕሮግራም ውስጥ የ92.3% ውጤታማነት እንዳገኘ አጢነዋል።

“የACPS ትምህርታዊ ማህበረሰብ፣ እንደ ካሳ ቺሪላጉዋ (Casa Chirilagua) እና ‘Liberty's Promise’ ባሉ የማህበረሰብ ድርጅቶች ውስጥ አጋር ሆኖ በመስራቱ-በጣም እድለኛ ነው፣” ብለዋል  በACPS ውስጥ፣ የማህበረሰብ አጋርነቶች እና ተሳትፎ ዋና-ዳይሬክተር - ከርት ኸፍማን (Kurt Huffman)። “በትብብር-የመስራት ግባችንን እንደ-ትምህርታዊ ኢኮሲስተ (educational ecosystem) አንዱ-አካል በመሆን — የማህበረሰብ አጋርነት፣ የትምህርት ቤት እና የክፍል (division) መሪነትን፣ ቤተሰቦችን፣ ተማሪዎች፣ ሠራተኞችን —በትምህርት እና በሁሉም የተማሪ ስኬቶች ውስጥ ፍትሃዊ-እኩልነት እንዲያገኙ ለማድረግ ያግዛሉ።

## አሁን-እስከ ኦክቶበር (Oct.) 2 ቀን 2022 ድረስ ክፍት-ነው: የትምህርት ቤት + የሕግ አስከባሪ አጋርነት የዳሰሳ-ጥናት



ያላችሁን አስተያየት (feedback)፣ በ'School + Law Enforcement Partnership (S+LEP) የዳሰሳ-ጥናት አማካኝነት እባካችሁ - አስገቡ። የዳሰሳ-ጥናቱ፤ ለቤተሰቦች፣ ሠራተኞች፣ እና ከ6-12 ክፍል ላሉ ተማሪዎች ለማጠናቀቅ ከ10-15 ደቂቃዎችን የሚወስድ እና፣ ከ'S+LEP Advisory Group' ጋር ስለ ትምህርት ቤት ደህንነት እና ጥበቃ አብሮ ለመስራት-ወሳኝ ነገር ነው።

የአሌክሳንድሪያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools (ACPS) ዋና-እሴቶቹ አድርጎ ያካተተው፤ ትምህርት ቤታችን ሁሉን የሚቀበል መሆኑን፣ እና ለሁሉም ሰው በደህንነት ተገኝቶ-የሚማርበት መሆኑን ማረጋገጥ ነው። ከዚህ የዳሰሳ-ጥናት የተገኙ ውጤቶች፤ የ'S+LEP Advisory Group'ን፤ በመጪው በዲሴምበር (December) 2022 - በACPS እና በአሌክሳንድርያ የፖሊስ መምሪያ መካከል እንደገና-እንዲታሰብ በታቀደው አጋርነት፣ ለትምህርት ቤት ቦርዱ ያቀረበውን የአስተያየት-ሃሳቦች ላይ፣ በቀጥታ ለመጠቀም ጥቅም-ላይ ይውላል። በተጨማሪም፤ የዳሰሳ-ጥናት ምላሽ-ሰጪዎች፣ በመጪው የ'focus group' ውይይቶች ላይ - ስለ ትምህርት ቤት እና ክፍሉ (division) ደህንነት እና ጥበቃ ላይ፣ ተካፋይ-የመሆን ፍላጎት እንዳላቸው የሚጠቁም ይሆናል።

ስለ 'S+LEP Advisory Group'፣ ተጨማሪ መረጃን ለማግኘት፤ እባካችሁ የACPS ድህረ-ገጽን ጎብኙ።

## የACPS የተማሪ አገልግሎቶች (Student Services) መምሪያ እና ፍትሃዊ-እኩልነት (Equity)፤ እንደ ፍትሃዊ-እኩልነት ልምዶች ዳይሬክተር አድርጎ - ብሪኤል ዌልሽ (Brielle Welch)ን ተቀብሏል



የአሌክሳንድሪያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools (ACPS)፤ ብሪኤል ዌልሽ (Brielle Welch)ን - ለክፍሉ/division - እንደ ፍትሃዊ-እኩልነት ልምዶች ዳይሬክተር ሆነው መመረጣቸውን ሲያሳውቅ-ደስታ ተሰምቶታል።

የACPS’ ምሩቃን (alumnus) የሆኑት - ዌልሽ (Welch) እንደ የፍትሃዊ-እኩልነት ባለሞያ እና በሌሎች ሰዎች ላይ ሰብዓዊነት በማየታቸው ኩራት የሚሰማቸው ሆነው፤ ይህን አመለካከት በየዕለታዊ ሕይወታቸው ውስጥ ሞዴል የሚያደርጉ ናቸው።

እንደ ፍትሃዊ-እኩልነት ባለሞያነታቸው፤ ዌልሽ (Welch) በስልጠና አማካኝነት - ይኸውም - ሳያውቁ-አድልዎ ማድረግ፣ ሁሉን-አካታች መሪነት፣ የዘር ጥቅም እና ማንነት እና በስራ-ቦታ አጋርነትን በመፍጠር፤ ባሉት-አማካኝነት፤ እውቀታቸውን የበለጠ አዳብረዋል። በ‘ስብጥር፣ በፍትሃዊ-እኩለነት እና ሁሉን አካታች (diversity, equity and inclusion (DEI)’ ላይ - ስርዓተ-ትምህርትን፣ አውደ-ጥናቶችን፣ ጽሁፎችን እና ዋና የማህበራዊ ሚዲያ ይዘትን በማዳበር - ፍትሃዊ-እኩልነትን እና ለሰዎች-ኃይል ሰጪነትን በማደበር - ከአምስት ዓመታት በላይ አሳልፈዋል። ከትምህርት እና የድርጅት-ደንበኞች ጋር በሦስት አህጉራቶች ውስጥ የሰሩ እና - ከዓለም-ዓቀፍ የገንዘብ-ድርጅቶች እስከ የስነጥበባት ትምህርት ሰጪ ካለ-ትርፍ የሚሰሩ (nonprofits) ድርጅቶች ባሉት-ሰፊ የድርጅት ዓይነቶች ውስጥ በማገልገል-ሰርተዋል። ዌልሽ (Welch)፤ ሁሉን ማንነቶች የደህንነት-ስሜት እንዲኖራቸው፣ ኃይል-ያላቸው ሆኖ እና እርዳታ-ያገኙ ሆኖ እንዲሰማቸው በማድረግ - በስራ-መስካቸው፣ በመማር-ተሞክሮአቸው እና በግል-እንቅስቃሴ-በማድረግ ላይ አዲስ ከፍተኛነት ስሜት እንዲኖራቸው - ሁሉንም መሪዎች ለማገዝ ቦታዎችን-በማዘጋቸው ቁርጠኛ-ናቸው።

ዌልሽ (Welch)፤ የባችለውር ኦፍ አርትስ (Bachelor of Arts) ዲግሪያቸውን በ‘Africana studies’ ከዊሊያም እና ሜሪ ኮሌጅ (College of William and Mary) ያገኙ እና፣ የማስተር ኦፍ አርትስ (Master of Arts) ዲግሪያቸውን በመጀመሪያ-ደረጃ ሁሉን አካታች ትምህርት - ከ‘Teachers College’፣ ከኮሎምብያ ዩኒበርስቲ (Columbia University) አግኝተዋል።

## የACPS የተማሪ አገልግሎቶች (Student Services) መምሪያ እና ፍትሃዊ-እኩልነት (Equity)፤ እንደ የትምህርት ቤት የጤና አገልግሎቶች ዳይሬክተር አድርጎ - ዶ/ር ሮቢን ዋሊን (Dr. Robin Wallin)ን ተቀብሏል



የአሌክሳንድሪያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools (ACPS)፤ ዶ/ር ሮቢን ዋሊን (Dr. Robin Wallin)ን እንደ - የክፍሉ/division የትምህርት ቤት የጤና አገልግሎቶች - ዳይሬክተር ሆነው መመረጣቸውን ሲያሳውቅ-ደስታ ተሰምቶታል። እንደ ዳይሬክተር ሆነው በትምህርት ቤት የጤና ክፍል - በቨርጅኒያ ውስጥ፣ ለፌር-ፋክስ ካንውቲ የጤና መምሪያ (Fairfax County Health Department) በቅርብ-ጊዜ ያገለገሉት፣ ዶ/ር ዋሊን (Dr. Wallin)፣ የ25 ዓመታት የስራ-ልምድን ወደ ትምህርት ቤቱ የጤና አገልግሎቶች የሚያመጡ ናቸው።

ዶ/ር ዋሊን (Dr. Wallin)፣ ከዚህ ቀደም እንደ የ‘ACPS ነርስ አስተባባሪ ሆነው በተማሪ አገልግሎቶች (Student Services) መምሪያ ውስጥ አገልግለዋል። እንደ የትምህርት ቤት ነርስ ሆነው፣ በዲስትሪክት ትምህርት ቤት የጤና መሪ እና የሕዝብ ጤና አስተዳደር ሆነው ሰርተዋል። በብሄራዊ ሰርቲፊኬሽን ቦርድ (National Certification Board) ለትምህርት ቤት ነርሶች ከ2015-18፣ እንደ የቦርድ ዳይሬክተሮች ሆነውም አገልግለዋል። ዶ/ር ዋሊን (Dr. Wallin)፣ ስር-የሰደደ የጤና ሁኔታዎች (chronic health conditions)ን በትምህርት ቤት ውስጥ እና በትምህርት ቤት ውስጥ-መሠረት ባደረገ የጤና እንክብካቤ አገልግሎቶች ውስጥ ለተማሪዎች በመቆጣጠር የተለየ-ፍላጎት ያላቸው ናቸው። ከበሽታ ቁጥጥር እና መከላከል ማዕከላት (Centers for Disease Control and

Prevention (CDC) ባልደረቦች ጋር በመሆን፣ ሁለት የጽሁፍ-ስራዎች በህትመት ያበረከቱ፣ እና የ'CDC Food AllergyToolkit - ለትምህርት ቤቶች' ላይ ቀደምት-ደራሲ ነበሩ።

ዶ/ር ዋሊን (Dr. Wallin)፣ በነርስ-ትምህርት የማስተር ኦፍ ሳይንስ (Master of Science) እና በ'nursing practice' ከየል ዩኒቨርስቲ (Yale University) ዶክትሬታቸውን አግኝተዋል። ፈቃድ-ያላቸው የሕፃናት ነርስ ፕራክትሽነር (pediatric nurse practitioner) እና በሃገር-ደረጃ በትምህርት ቤት ነርስነት ፈቃድ-ያላቸው ናቸው።

## ብሄራዊ የስነ-ጥበባት (National Arts)፣ በትምህርት ሣምንት ውስጥ: ተሣተፉ እና የACPS የትወና-ስነጥበባትን (Performing Arts) ደግፉ



ስነጥበብ (Art)፤ ተማሪዎች በፈጠራ፣ በርህራሄ፣ እና ችግሮችን መፍታት ችሎታዎች እንዲያድጉ፤ እንዲሁም በተጨማሪ - የደስታ እና የመዝናኛ ምንጭም ሊሆን የሚችል አስፈላጊ ነገር ነው። የ'ብሄራዊ የስነ-ጥበባት (National Arts)፣ በትምህርት ሣምንት'ን ጨርሰን በምንዘጋበት ወቅት፤ ሁሉንም የአሌክሳንድሪያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools (ACPS) ቤተሰቦችን - በሙዚቃ እና በቲያትር ዙሪያ፣ የተማሪዎቻችንን ትዕይንቶች እንዲደግፉ እናበረታታለን።

የአሌክሳንድሪያ ከተማ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (Alexandria City High School (ACHS) - የ'Fall Play' የጊዜ-ሰሌዳ - በኖቬበር ውስጥ - ከሁለት ሞደርን ኮሜዲዎች — "One Slight Hitch" እና "Chicken and Biscuits" ጋር የሚካሄድ-ይሆናል። ትዕይንቶቹ፣ በትምህርት ቤቱ የስብሰባ-አድራሽ/ኦዲተሪየም (auditorium) ውስጥ የሚሆን-እና፣ የጊዜ-ሰሌዳው እንደሚከተለው ቀን ይሆናል:

"One Slight Hitch"

- አርብ፣ ኖቬምበር (Nov.) 11 ቀን፣ በ7:30 p.m.
- ቅዳሜ፣ ኖቬምበር (Nov.) 12 ቀን፣ በ7:30 p.m.
- እሁድ፣ ኖቬምበር (Nov.) 13 ቀን፣ በ3 p.m.

"Chicken & Biscuits"

- ሐሙስ፣ ኖቬምበር (Nov.) 17 ቀን፣ በ7:30 p.m.
- አርብ፣ ኖቬምበር (Nov.) 18 ቀን፣ በ7:30 p.m.
- ቅዳሜ፣ ኖቬምበር (Nov.) 19 ቀን፣ በ7:30 p.m.

ወደፊት በመግፋት-በምንመለከት ጊዜ፤ የACHS የድራማ አስተማሪ ሊስሌ ጆንስ (Leslie Jones)፣ ስለ 'one-act play festival' በጃንዋሪ ውስጥ፣ እና በፀደይ የሙዚቃ በኤፕሪል (April) ወር ውስጥ - ስለሚካሄደው መረጃዎችን እየተከታተሉ እንዲቆዩ ተናግረዋል።

የ‘ACHS’ የኦርኬስትራ (orchestra) ፕሮግራም፤ ቬሮኒካ ጃክሰን (Veronica Jackson) የኦርኬስትራ ዳይሬክተር ሆነው ቦታውን ከተረከቡበት - ከትምህርት ዓመት 2020-21 ወቅት ጀምሮ፤ ከ80 ተማሪዎች ወደ 150 የሚጠጉ ተማሪዎች አድጓል። ጃክሰን (Jackson)፤ እንደ የኦርኬስትራ (orchestra) ዳይሬክተር ሆነው ለስምንት ዓመታት በፍራንሲስ ሲ. ሃመንድ (Francis C. Hammond) መካከለኛ ደረጃ (Middle) ትምህርት ቤት ውስጥ በማስተማር፣ ለACPS የመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የኦርኬስትራ አስተማሪዎች ክሬዲቶችን በመውሰድ ሰርተዋል።

የኦርኬስትራው (orchestra) ኮሰርቶች፤ በኦክቶበር (October) ወር ውስጥ ለመጀመር የጊዜ-ሰሌዳ የተያዘለት እና ሁሉም ትዕይንቶች በ7 p.m. በACHS የሚካሄዱ ሲሆን፤ ከዚህ በታች በተዘረዘሩት-መሰረት በሌላ-ሁኔታ ካልቀረበ በስተቀር-ይካሄዳሉ:

- ሐሙስ፣ ኦክቶበር (Oct.) 20 ቀን
- ሮብ፣ ኦክቶበር (Oct.) 26 ቀን
- ሐሙስ፣ ዲሴምበር (Dec.) 8 ቀን
- ሮብ፣ ፌብሩዋሪ (Feb) 15 ቀን፣ (በ6 p.m.)
- ማክሰኞ፣ ፌብሩዋሪ (Feb.) 28 ቀን (በትምህርት ቀኑ ወቅት)
- ሐሙስ፣ ሜይ (May) 4 ቀን

የACHS የኦርኬስትራ (orchestra) ፕሮግራምን፣ በFacebook page ተመልከቱት፣ ለተጨማሪ መረጃ ወይም ለማነጋገር በ achsorch@gmail.com ኢሜል አድርጉ።

የቲታን ኩዋየር (Titans Choir) የሚከተሉትን ት ዕይንቶችን - ሁሉም በACHS የስብሰባ-አዳራሽ/ኦዲተሪየም (auditorium) ውስጥ የሚካሄድ-ሆኖ የጊዜ-ሰሌዳ ወጥቶለታል:

- የበልግ ኮንሰረት (Fall Concert): ሮብ፣ ኦክቶበር (Oct.) 26 ቀን፣ በ7 p.m.
- የኳየር የክረምት ኮንሰርት (Choir Winter Concert): ማክሰኞ፤ ዲሴምበር (Dec.) 13 ቀን፣ በ7:30 p.m.
- የኳየር የፒራሚድ ኮንሰርት (Choir Pyramid Concert): ሮብ፣ ማርች (March) 1 ቀን በ6:30 p.m.
- የኳየር የፀደይ ኮንሰርት (Choir Spring Concert): ሐሙስ፤ ጁን (June) 1 ቀን፣ በ7:30 p.m.

ለተጨማሪ መረጃ፤ የ www.titanschoir.org፣ @titanschoir በኢንስተግራም (Instagram) ላይ ወይም @ACTitansChoir በ ትዊተር (Twitter) ላይ፤ ጎብኙ።

## የ'Back to School’ ቅጾችን በኦንላይን - አጠናቅቆ-መሙላት፤ በተማሪዎ ትምህርት ላይ መሣተፍ



በተማሪዎ ትምህርት ላይ፣ ኃይል-እንዳላችሁ ሆኖ እንዲሰማችሁ እና ተሳትፎ-ማድረግን ትፈልጋላችሁ? የተማሪዎን የ‘Back to School’ ቅጾችን - ‘PowerSchool’ን በመጠቀም ትክክለኛነቱን ማረጋገጥ፣ በትምህርታቸው ላይ ንቁ-የሆነ ሚናን ለመጫወት - የመጀመሪያው እርምጃ ነው። እነዚህ ቅጾብ እስከ ሴፕቴምበር (Sept.) 30 ቀን 2022 ድረስ ሞልቶ-በማጠናቀቅ፤ አስተማሪዎች እና ሠራተኞች ትክክለኛ-

የሆነ የመገኛ መረጃዎች እንዲኖራቸው የሚያረጋግጥል ሲሆን፣ ከቤተሰቦች ጋር ስለ ቀለም-ትምህርት እድገት እና የሚያስፈልግ እርዳታ ከቤተሰቦች ጋር ስለተማሪው ስኬታማነት - የሚያሳትፈን ይሆናል።

ማድረግ-የሚገባችሁ፤ አንድ የመግቢያ (login) እና የመግቢያ-ኮድ (password) ብቻ ሲሆን፤ የኦንላይን ፖርታል ላይ የሚስተካከል የመገኛ-አድራሻችሁን እና ሌላ ጠቃሚ-የሆነ መረጃን ማስተካከል የምትችሉበት ነው። ምንም-እንኳን መረጃችሁ -ካለፈው ዓመት ያልተቀየረ-ቢሆንም እንኳን፤ ትክክለኛ-መሆኑን እንድታረጋግጡልን እና አስፈላጊ-የሆኑ ማስተካከያዎችን እንድታደርጉ፤ በተለይ-ደግሞ - በአደጋ-ጊዜ መገኘት የሚችሉ ሰዎች አድራሻዎችን እና የተማሪ የጤና መረጃን በደንብ-እንድትመለከቱት እና እንድታረጋግጡልን እንፈልጋለን።

የእንግሊዘኛ እና የስፓኒሽ-ቋንቋ ተናጋሪ ቤተሰቦቻችን - በኤሌክትሮኒክ ዲቫይስ (electronic device) ላይ፤ አስፈላጊ የሆኑትን ቅጾች በ‘PowerSchool’ ውስጥ ለመሙላት - ከዚህ በታች-ያለውን ማገናኛዎች (links) እንዲጠቀሙ-እንጠይቃለን:

- እንግሊዘኛ/English 2022-23 የ‘Back to School’ ቅጾች።
- ስፓኒሽ/Spanish 2022-23 የ‘Back to School’ ቅጾች።

የአማርኛ - እና አረብኛ-ቋንቋ ተናጋሪ ቤተሰቦቻችን፤ ዳውንሎድ ተደርጎ የታተመውን የBack to School’ ጥራዝ/packetን - በኦንላይን ላይ በአማርኛ እና አረብኛ የሚገኘውን-በመሙላት፤ ወይም ጥራዙን (a packet) - ከልጃቸው ትምህርት ቤቶች በመጠየቅ ሊያጠናቅቁ-ይችላሉ። እንግሊዘኛ- እና ስፓኒሽ-ቋንቋ ተናጋሪ ቤተሰቦች - የኤሌክትሮኒክ ዲቫይስ የሌላቸው ከሆኑም፤ ዳውንሎድ ተደርጎ የታተመውን የBack to School’ ጥራዝ/packetን - በኦንላይን ላይ በእንግሊዘኛ/English እና ስፓኒሽ የሚገኘውን-በመሙላት፤ ወይም ከትምህርት ቤታቸው የታተመውን ጥራዝ (a packet) በመጠየቅ፣ ማጠናቀቅ-ይችላሉ። ተሞልቶ-የተጠናቀቁ ቅጾች፤ ወደ ትምህርት ቤቱ የእንግዳ መቀበያ ቢሮ (front office) መግባት-አለባቸው።

## የሴፕቴምበር (Sept.) 22 ቀን 2022 - የትምህርት ቤት ቦርድ አጀንዳ



የትምህርት ቤት የቦርድ፣ የሚቀጥለው ስብሰባ፤ ሴፕቴምበር (Sept.) 22 ቀን 2022 ይሆናል። የትምህርት ቤት የቦርድ ስብሰባ አጀንዳዎችን እና ሰነዶችን ለማግኘት፤ Electronic School Boardን ይጎብኙ። ስብሰባዎችን በቀጥታ ለመመልከት እና ለመካፈል እንዴት እንደሚችሉ መረጃዎችን ለማግኘትም፤ በትምህርት ቤት ቦርድ ስብሰባ ድህረ-ገጽ መጎብኘት ትችላላችሁ።

# በሴፕቴምበር (Sept.) 8 ቀን 2022 - የአሌክሳንድርያ የCOVID-19 ማህበረሰብ ያለበት ደረጃ




እስከ ሴፕቴምበር (Sept.) 8 ቀን 2022 - ባለው-ጊዜ፤ የአሌክሳንድርያ ከተማ የCOVID-19 ማህበረሰቡ-የሚገኝበት ደረጃ - ዝቅተኛ/low ሲሆን፤ ባለፉት ሰባት ቀናቶች ውስጥ፤  በየ100,000 ሰዎች፣ 160.0 ታማሚዎች አሉት። የበለጠ ለማወቅ፤ Alexandria COVID-19 dashboard ጎብኙ።

የመረጃ-ስብስቡ (data)፤ በመጨረሻ-እንዲስተካከል የተደረገው በሴፕቴምበር (Sept.) 8 ቀን 2022 ላይ እንደሆነ፣ እባካችሁ አስታውሱ። የበሽታ ቁጥጥር እና መከላከል ማዕከል (Center for Disease Control and Prevention)፤ በሦስት ሜትሪክስ (three metrics) ጥምሮች ውስጥ - የCOVID-19 የማህበረሰብ የደረጃ-መጠንን ለመወሰን ተመልክቷል: አዲስ የCOVID-19 ታማሚ ሆነው የተመረመሩበትን በ100,000 የሕዝብ-ቁጥር/population - በአለፉት ሰባት ቀናት ውስጥ፤ ገብተው-የተኙ በCOVID-19 ታካሚዎች የተያዙ አልጋዎች - በእያንዳንዱ የCOVID-19 በሽተኛ-ቁጥር፤ እና አጠቃላይ አዲስ የCOVID-19 ታማሚዎችን በየ100,000 የሕዝብ-ቁጥር/population - በአለፉት ሰባት ቀናት ውስጥ ተመልክቷል።